የሰ/መ/ቁጥር---216240
ቀን- ጥር 24 ቀን 2015 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ብርሃኑ አመነዉ
በዕዉቀት በላይ
በቀነዓ ቂጣታ
ሌሊሴ ደሳለኝ
ኑረዲን ከድር

**አመልካቾች፡-** 1. አቶ ተገኔ ዘሪሁን
2. ወ/ሮ ትርንጎ ተመስገን } አልቀረቡም
3. አቶ ሽመልስ ገላን

**ተጠሪዎች፡-** 1. አቶ ዘሪሁን ተመስገን
2. ወ/ሮ አስቴር ቶማ } አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው የፍርድ አፈጻጸምን የተመለከተ ጉዳይ ሲሆን የተጀመረው በሀዋሳ አካባቢ ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪዎች እንደቅደም ተከተላቸዉ የአፈጻጸም ከሳሽና የአፈጻጸም ተከሳሾች ሲሆኑ የአሁን አመልካቾች ደግሞ የአፈጻጸም ንብረቱ እንደሚመለከታቸዉ በመግለጽ አቤቱታ ያቀረቡ ጣልቃ ገቦች ነበሩ፡፡ የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ የሀዋሳ አካባቢ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 33019 ጥር 29 ቀን 2012 ዓ.ም ተሰጥቶ በሲዳማ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በትዕዛዝ ያጸናዉ የአፈጻጸም ብይን እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደግሞ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለኝም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉ ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በሚል ነዉ፡፡

የክርክሩ አመጣጥ፡- በስረ ነገሩ ጉዳይ የአሁን አመልካቾች የሟች አያታቸዉ የአቶ ተመስገን በዛብህ ተተኪ ወራሾች መሆናቸዉን ገልጸዉ ተጠሪዎች በእጃቸዉ ያለዉን የማይንቀሳቀሱና የሚንቀሳቀሱ ንብረቶችን ዘርዝረዉ እንዲያካፍሏቸዉ ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን የሀዋሳ አካባቢ ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ በመ/ቁ 33019 ታሕሳስ 24 ቀን 2007 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት ጉዳዩን መርምሮ ግራ ቀኙ በተለያዩ መዛግብት ሲከራከሩ የቆዩ ዉሳኔም ሲሳጥበት የቆየ መሆኑን በማተት 1ኛ ሲዳማ ዞን ወንዶ ገነት ወረዳ ዉስጥ ወተራ እና ቀጨማ ቀበሌ ያለዉ በ2ኛ ተጠሪ እጅ የሚገኘዉ የመሬት ይዞታና ቤት እና 2ኛ በኦሮሚያ ክልል በአርሲ

ዞን ኮፈሌ ወረዳ ጉች ቀበሌ በ1ኛ ተጠሪ እጅ የሚገኝ ይዞታ፣ ሳር ቤትና ከብት የዉርስ ሀብት በመሆናቸዉ አስቀድሞ በወንዶ ገነት ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 06166 ግንቦት 18 ቀን 2000 ዓ.ም ተጠሪዎች እንዲካፈሉት የተሰጠዉ ዉሳኔ ቢኖርም ግራ ቀኙ እኩል እንዲካፈሉት ወስኗል፡፡ ሆኖም ወ/ሪት መታሰቢያ ለገሰ በዉሳኔዉ ቅር ተሰኝተዉ ባቀረቡት ይግባኝ መነሻነት ጉዳዩን የተመለከተዉ የደቡብ ብ/ብ/ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 64300 ግንቦት 21 ቀን 2007 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት ጉዳዩን መርምሮ የአሁን አመልካቾች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ጉዳይ ከዚህ በፊት አቅርበዉ የመብት ጥያቄያቸዉ ዉድቅ ተደርጎ የይግባኝ ሂደቱን አሟጠዉ መጨረሳቸዉን እያወቁ ከቅን ልቦና ዉጪ በድጋሚ ይህንኑ በፍርድ ያለቀን ጉዳይ ክስ አቅርበዉ ያስወሰኑት ነዉ በማለት የዞኑን ከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡ በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ ያቀረቡት ይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡

ለአሁኑ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነዉ የሀዋሳ አካባቢ ከፍተኛ ፍ/ቤት በአሁኑ ተጠሪዎች መካከል የዉርስ ሀብት ክፍፍል አፈጻጸም በሂደት ላይ ባለበት የአሁን አመልካቾች ታሕሳስ 13 ቀን 2012 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ በተጠሪዎች መካከል እየተካሄደ የሚገኘዉ የዉርስ ሀብት ክፍፍል አፈጻጸም አመልካቾችንም ጭምር የሚመለከታቸዉ መሆኑን ገልጸዉ ክፍፍል እንዲደረግላቸዉ የጠየቁ ሲሆን ፍ/ቤቱ የአሁን ተጠሪዎችን አስተያየት ከተቀበለ በኃላ መርምሮ በወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 06166 እና 05148 በሆኑት መዝገቦች በተደረገዉ የአፈጻጸም ክርክር መብት አለን በማለት አቅርበዉ ዉድቅ ተደረጎባቸዉ ለከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበዉ በመ/ቁ 25131 ነሐሴ 29 ቀን 2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት መብት እንዴሌላቸዉ ተገልጾ ብይን የተሰጠ መሆኑን፤ አሁንም ከተሰጠዉ ብይን የተለዬ ነገር በሌለበት መብት አለን በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት የለዉም በማለት ዉድቅ ሲያደርግ ተጠሪዎችን ላጉላሉበት ኪሳራ ብር 600 እንዲከፍሉ ብይን ሰጥቷል፡፡ በዚህ ብይን ቅር ተሰኝተዉ አመልካቾች ለሲዳማ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ በመቀጠል ለክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ቢያቀርቡም ግራ ቀኙ የተለያዩ ክልል ነዋሪዎች በመሆናቸዉና ጉዳዩ የፌዴራል በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1234/13 አንቀጽ 5(1/ሸ) እና በፌዴራሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 80(3/ለ) መሰረት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለኝም በማለት በትዕዛዝ አሰናብቷል፡፡ አመልካቾች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ይህን የአፈጻጸም ብይን/ትዕዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአመልካቾች ሕዳር 06 ቀን 2014 ዓ.ም የተዘጋጀ 6 ገጽ ሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፡- የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 33019 ታሕሳስ 24 ቀን 2007 ዓ.ም ጉዳዩ የፌዴራል በመሆኑ በዉክልና ስልጣኑ የሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ ሆኖ እያለ ከዚያ በፊት ስልጣን የሌለዉ የወንዶ ገነት ወረዳ ፍ/ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በመጥቀስ በመ/ቁ 06166 ግንቦት 18 ቀን 2000 የተሰጠዉ ዉሳኔ ይፈጸም በማለት ከፍተኛዉ ፍ/ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 63295 መስከረም 28 ቀን 2007 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሁለት ክልል ነዋሪዎች መካከል የተነሳዉን ክርክር ዓይቶ ለመወሰን ስልጣን የሌለዉ የወረዳ ፍ/ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በመጥቀስ ዉሳኔዉን መሻሩ ተገቢ ባለመሆኑ ስህተቱ ሊታረም ይገባል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤትም በመ/ቁ 115121 ሐምሌ 15 ቀን 2007 ዓ.ም እነዚህን

ዉሳኔዎች ማጽናቱ ስህተት ነዉ፡፡ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 117630 የሰጠዉ ትዕዛዝም ስህተት ነዉ፡፡ ስለሆነም ጉዳዩን አከራክሮ ዉሳኔ ለመስጠት ስልጣን ያልተሰጠዉ የወንዶ ገነት ወረዳ ፍ/ቤት የተሰጠዉ ዉሳኔ የሕግ ስህተት ያለበት ነዉ ተብሎ ተሽሮ በዉክልና ስልጣን የተሰጠዉ የቀድሞ የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 33019 ታሕሳስ 2007 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እንዲፈጸም እንዲወሰንላቸዉ ጠይቀዋል፡፡

የአመልካቾች አቤቱታ ተመርምሮ በዋናዉ ክርክር ዉሳኔ ባገኘበት በአፈጻጸም ደረጃ ላይ ደርሶ አፈጻጸም ችሎቱ ስልጣን የለኝም የማለቱን አግባብ ከአጠቃላይ ክርክር አመራር እና ሥነ-ሥርዓት አንጻር ለማጣራት ሲባል መዝገቡ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል የተባለ ነዉ፡፡

1ኛ ተጠሪ ሚያዚያ 07 ቀን 2014 ዓ.ም የተዘጋጀ 3 ገጽ መልስ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱ በአጭሩ፡- አመልካቾች እስከመጨረሻዉ ተከራክረን ዉሳኔ ያገኘዉን ጉዳይ መልሰዉ በአፈጻጸም ጉዳይ ማንሳታቸዉ ሥነ-ሥርዓታዊ አይደለም፡፡ አመልካቾች የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 33019 ታሕሳስ 24 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እንዲፈጸምላቸዉ መጠየቃቸዉ ተገቢ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ዉሳኔዉ ተሽሮ ፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ በጸናበት ሕግ ከሚፈቅደዉ ዉጪ አስቀድሞ የተሰጠዉ ዉሳኔ የሚቀየርበት አግባብ ባለመኖሩ የሰበር አቤቱታቸዉ ዉድቅ እንዲደረግ በመጠየቅ ተከራክረዋል፡፡

2ኛ ተጠሪ በበኩላቸዉ መጋቢት 14 ቀን 2014 ዓ.ም የተዘጋጀ 5 ገጽ መልስ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም በአጭሩ፡- አመልካቾች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ጉዳይ ከዚህ ቀደም እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበዉ የመብት ጥያቄያቸዉ ዉድቅ ተደርጎ በተጠናቀቀ ጉዳይ ከቅን ልቦና ዉጪ የሚያቀርቡት ክርክር በመሆኑ ጉዳዩ አስቀድሞ የታየባቸዉን 6 መዝገቦች ቀርበዉ እንዲታይላቸዉና አመልካቾች የሰበር አቤቱታቸዉ ዉድቅ እንዲደረጉ በመጠየቅ ተከራክረዋል፡፡

1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ሚያዚያ 28 ቀን 2014 ዓ.ም የተዘጋጀ 6 ገጽ እንዲሁም ሚያዚያ 28 ቀን 2014 ዓ.ም ተዘጋጀ 3 ገጽ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸዉን በሚያጠናክር መልኩ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን እኛም አቤቱታ ከቀረበበት የአፈጻጸም ብይን እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡ መርምረን እንደተረዳነዉ አመልካቾች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ አጥብቀዉ የሚከራከሩት የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 33019 ታሕሳስ 24 ቀን 2007 ዓ.ም የሟች አቶ ተመስገን በዛብህ የዉርስ ሀብት የሆኑትን በሲዳማ ዞን ወንዶ ገነት ወረዳ ወተረና ቀጫማ ቀበሌ ዉስጥ የሚገኝ የእርሻ መሬት ይዞታና ከብት እንዲሁም በአርሲ ዞን ከፊሌ ወረዳ ጉቺ ቀበሌ ዉስጥ የሚገኝ የእርሻ መሬትና የከብት መዋያ ይዞታ በወንዶ ገነት ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 06166 ግንቦት 18 ቀን 2000 ዓ.ም በተሰጠዉ ብይን መሠረት ግራ ቀኙ እኩል እንዲካፈሉ በተሰጠዉ ዉሳኔ መሠረት የዉርስ ሀብት ክፍፍሉ የሚመለከተዉ ተጠሪዎችን ብቻ ሳይሆን አመልካቾችንም ጭምር በመሆኑ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔ እንዲፈጸምላቸዉ ነዉ፡፡

አመልካቾች በሰበር አቤቱታቸዉ እንዲፈጸምላቸዉ የጠየቁት የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 33019 ታሕሳስ 24 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ በደቡብ ብ/ብ/ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 64300 ግንቦት 21 ቀን 2007 ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ አስቀድሞ በወንዶ ገነት ወረዳ ፍ/ቤት በተሰጠና በየደረጃዉ የጸና ዉሳኔ ባለበት የተሰጠ ፍርድ ነዉ በሚል የተሻረ መሆኑን፤ ይህን የተሻረበትን ዉሳኔ ለማስለወጥ አመልካቾች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም በመ/ቁ 115121 ሐምሌ 15 ቀን በተሰጠ ትዕዛዝ መጽናቱን እንዲሁም የሰበር አቤቱታ አቅርበዉ ፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 117630 ሕዳር 02 ቀን 2008 ዓ.ም ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም በሚል መጽናቱን አረጋግጠዋል፡፡ ይህ ችሎትም የሰ/መ/ቁ 117630 ን በማስቀረብ ይህንኑ ተመልክቷል፡፡ አመልካቾች የተሻረዉ ዉሳኔ እንዲፈጸምላቸዉ ላቀረቡት አቤቱታ በመከራከሪያነት ያቀረቡት ለዉሳኔዉ መሻር ምክንያት የሆነዉ የወንዶ ገነት ወረዳ ፍ/ቤት በሁለት ክልል ነዋሪዎች መካከል የተነሳንና የፌዴራል ጉዳይ የሆነን ክርክር ተመልክቶ ዉሳኔ ለመስጠት ስልጣን ሳይኖረዉ በመ/ቁ 06166 ጉዳዩን ተመልክቶ የሰጠዉ ዉሳኔ በመሆኑ ለዚህ ዉሳኔ እዉቅና በመስጠት በየደረጃዉ ባሉት ፍ/ቤቶች አስቀድሞ የተፈጸሙት ስህተቶች ሊታረሙ ይገባል በሚል ነዉ፡፡

በመሰረቱ አንድ ፍ/ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ ይግባኝ ሰሚዉ ፍ/ቤት በሥነ-ሥርዓት ሕጉ በተቀመጠዉ ሥርዓት መሠረት ግራ ቀኙን አከራክሮ ከሻረዉ በኃላ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 314፣ 320(1)፣ 327 እና ሌሎች የሥነ-ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች መሠረት ይግባኝ ቀርቦበት ካልተሻረ በቀር ይግባኝ ሰሚዉ ፍ/ቤት ለዉሳኔዉ መሠረት ያደረገዉ ምክንያት ተገቢነት የለዉም ወይም ዉሳኔዉ ስልጣን በሌለዉ ፍ/ቤት የተሰጠ ዉሳኔን መሠረት ያደረገ ነዉ በሚል ብቻ ዉሳኔዉ ዋጋ የሚያጣበትና የመጀመሪያዉ ፍ/ቤት ዉሳኔ ሕይወት የሚዘራበት ወይም ተፈጻሚ የሚሆንበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 212 ድንጋጌ በግልጽ በይግባኝ ታይቶ እንዲታረም ካልተደረገ በስተቀር የተሰጠ ዉሳኔ አስገዳጅነትና የመጨረሻ ዉሳኔ መሆኑ ተመላክቷል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 85718 በሰጠዉ ዉሳኔ አንድ ጉዳይ ለማየት በሕግ ስልጣን በሌለዉ ፍ/ቤት ታይቶ የተሰጠ ዉሳኔ በይግባኝ ታይቶ እንዲታረም ካልተደረገ በቀር በጉዳዩ ላይ አስገዳጅነት ያለዉ ስለመሆኑ ገዥ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለዉ ስልጣን የሌለዉ ፍ/ቤት ጉዳዩን ተመልክቶ የሰጠዉ ዉሳኔ በይግባኝ ወይም በሰበር ሰርዓት ታይቶ እስካልታረመ ድረስ ዋጋ የሚያጣበት ወይም ዉሳኔዉን ተመርኩዞ የተሰጠ ዉሳኔ ዋጋ አልባ ነዉ የሚባልበት የሕግ አግባብ የለም፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ የአመልካቾች አያት የሆኑት የሟች አቶ ተመስገን በዛብህ የዉርስ ሀብት ክፍፍልን አስመልክቶ የወንዶ ገነት ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 06166 ግንቦት 18 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ በአመልካቾች ጠያቂነት ስልጣን በሌለዉ ፍ/ቤት የተሰጠ ዉሳኔ ነዉ በሚል እንዲሻር ባልተደረገበት እንዲሁም አመልካቾች የዉርስ ሀብት ይገባናል በማለት ያቀረቡትን ክስ ተከትሎ የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 33019 ታሕሳስ 24 ቀን 2004 ዓ.ም አመልካቾች ከዉርስ ሀብቱ እኩል እንዲከፈሉ ተሰጥቶ የነበረዉ ዉሳኔ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በይግባኝ ሰሚዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 64300 ግንቦት 21 ቀን 2007 ዓ.ም በተሰጠ ዉሳኔ በተሻረበት እና አመልካቾች ይህንኑ ዉሳኔ ለማሻር ያቀረቡት የይግባኝና የሰበር አቤቱታዎች ዉድቅ በተደረጉበት ሁኔታ ተጠሪዎች በፍርድ በተረጋገጠላቸዉ ዉሳኔ እየተካሄደ ባለዉ የፍርድ አፈጻጸም ሂደት አመልካቾች የተሻረዉ የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 33019 ታሕሳስ 24 ቀን 2004 ዓ.ም የተሰጠዉ ዉሳኔ ይፈጸምልን በማለት የሚያቀርቡት አቤቱታ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አስቀድሞ ታይቶ በፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 117630 ሕዳር 02 ቀን 2008 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ የጸናዉን ዉሳኔ ስህተት የተፈጸመበት ቢሆን እንኳ ይህ ችሎት በተያዘዉ መዝገብ ሊያርም የሚችልበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ ስለሆነም የሀዋሳ አካባቢ ከፍተኛ ፍ/ቤት የአመልካቾችን አቤቱታ በተደጋጋሚ ዉድቅ በተደረገ ጉዳይ የተፈጠረ የተለየ ሁኔታ በሌለበት የቀረበ አቤቱታ ነዉ በማለት ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉ የአፈጻጸም ብይን የሚነቀፍበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡

ሲጠቃለል የስር ፍ/ቤት አመልካቾች በአፈጻጸም ጉዳዩ መብት አለን ሲሉ ያቀረቡትን አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉ የአፈጻጸም ብይን መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት ባለመቻሉ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

## ዉሳኔ

1. በሀዋሳ አካባቢ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 33019 ጥር 29 ቀን 2012 ዓ.ም ተሰጥቶ በሲዳማ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 00708 ግንቦት 24 ቀን 2013 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ የጸናዉ የአፈጻጸም ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
3. መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ዉሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም